

መልክዐ ቅዱስ ሱርያል-ግዕዝ

፩. ሰላም ለዝክረ ስምከ ሱርያል መልአክ፤ እምድኅረ ፀዓድው አርባዕ ዘፈነወከ መልአክ፤ ነገረ ምሥጢር ትዜኑ ለወልደ ላሜክ፤ ማኅተተ ስምከ ከመ ኢይኩን በበክ፤ ጊዜ ጐሐ ጽባሕ አጽምእ ወዓዲ በሠርክ።

፪. ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ እምነ ጠባዕይ ክልኤቱ፤ እንተ ዘኮነ ፍጥረቱ፤ ሱርያል መልአክ አንተ ውእቱ፤ ጸዋሬ ብሥራት እምነ ፀዓድው ሠለስቱ፤ እንተ ሐወጽከመ ድኅረ ለእግዚእ እምቤቱ።

፫. ሰላም ለርእስከ መካነ ልብከ ለባዊ፤ ነገረ ምሥጢር ሱርያል ለወልደ ላሜክ ዜናዊ፤ አስተምሕር ሊተ ኀበ አምላክ ማሕየዊ፤ እትከለል ወልታ አክናፊከ እምገጸ አርዌ ነዓዊ፤ በግዕ ድኩም ለጽኑስ ኖላዊ።

፬. ሰላም ለላህየ ገጽከ ዘጥቀ ይልሂ፤ እምጸዳለ መብረቅ ስቡሕ ወእምስነ ፀሐይ መብርሂ፤ ዕበየ አምላክ ሱርያል ዘእንበለ ዕረፍት ሰባሒ፤ እምነፋሰ ዐውሎ ጊዜ ፈቀደ ይበርሂ፤ ላህየ ገጽከ ገጽየ ያጽግሂ።

፭. ሰላም ለቀራንብቲከ ዘኢየአምራ ድካመ፤ ወዓዲ ንዋመ፤ ሱርያል በመስቀረ ዕዕ ዘሐደፍከ ዓለመ፤ ማሕሌትየ በእደ ዚኣከ ትትመሠጥ አርያመ፤ ከመ ታምጽእ ሊተ ብዙኀ ሰላመ።

፮. ሰላም ለአዕይንቲከ እለ ይኔጽራ ዘልፈ፤ መድምማተ አምላክ ትሩፈ፤ ሰንሰሪቁ መብረቅ ሱርያል እንተ ረሰይከ ዐዕፈ፤

የቅዱስ ሱርያል መልክዕ በአማርኛ

1. ለዝክረ ስምከ፡- ለስም አጠራርህ ሰላምታ ይገባል፤ ለላሜክ ልጅ የምሥጢርን ነገር ትነግር ዘንድ ከአራቱ ነፋሳት በኋላ አምላክ የላከህ መልአኩ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ምስጋና ለከንቱ እንዳይሆን በነግህ ጊዜ አድምጥ፤ ዳግመኛም በሠርክ አድምጥ።

2. ለሥዕርተ ርእስከ፡- ተፈጥሮው ከኹለቱ ባሕርያት ለሆነው ለራስህ ጠጕር ሰላምታ ይገባል፤ መልአኩ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከጌታ ወገኖች በኋላ ከጐበኘኻቸው ከሦስቱ ነጫፍሳት ይልቅ የምሥራችን የተሸከምህ አንተ ነህ።

3. ለርእስከ፡- የልብህን ማዕከል ልብ ለሚያደርግ ለራስህ ሰላምታ ይገባል፤ ለላሜክ ልጅ የምሥጢርን ነገር ትነግር ዘንድ የአበሠርህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የችግረኛ እረኛ ደካማው በግ እኔ ከአዳኝ አውሬ ፊት የክንፎችህን ጋሻ እጋረድ ዘንድ ወደሚያድነው አምላክ ማልድልኝ።

4. ለላህየ ገጽከ፡- ከሚያንጸባርቅ ከመብረቅ ፀዳል እና ከሚያበራ ከፀሐይ ውበት ይልቅ እጅግ ለሚያበራው ለፊትህ ወዝ ሰላምታ ይገባል፤ ያለ ዕረፍት የምታመሰግን አምላክ ከፍ ከፍ የአደረገህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከዐውሎ ነፋስ የተነሣ በራ ሊሆን (ሊመለጥ) በወደደ ጊዜ የፊትህ ወዝ ፊቴን ያለምልም።

5. ለቀራንብቲከ፡- ድካምንና ዳግመኛም እንቅልፍን ለማያውቁ ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል፤ ዓለምን በመስቀል መቅዘፊያ የአሻገርህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ለእኔ ብዙ ሰላምን ታመጣልኝ ዘንድ ምስጋናዬ በአንተ ሥልጣን ወደ አርያም ትነጠቅ።

6. ለአዕይንቲከ፡- አምላክ የሚደነቅባቸው ትሩፋትን ዘወትር ለሚያዩ ዐይኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ የመብረቅን ግምጃ መጐናጸፊያ የአደረግህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ!

ከሠተ ማሕሌተ ስምከ በሃመ አፈ፡ ወአስተናግረ ልሳነ ጸያፈ፡፡

፮. ሰላ ለአእዛኒከ እለ ያጸምኣ ወትረ፡ እምአፈ ፀባያት ዘወፅአ ግሩመ ነገረ፡ ለወልደ ላሜክ ሱርያል ዘአለበውኮ ምሥጢረ፡ እምነ ሕዝብየ ከመ አይኩን ነኪረ፡ አንሰ አጥረይኩ ኪያከ ማእምረ፡፡

፯. አስትአ ማሕሌት አቁርብ ለመላትሒከ በጽሒቅ፡ ፍሬ ከናፍርየ አንሰ ከመ ንዋየ ብሩር ወወርቅ፡ ሱርያል ሊቅ ዘታዕካ ሰማይ ማዕነቅ፡ ዕቀበኒ ኢይንድፈኒ በሐፀ ቅንአቱ ውሱቅ፡ ዲበ ኖፃ ባሕር ዘቆመ መብረቅ፡፡

፰. ሰላ ለአእናፈከ እለ ያጼንዋ ወያስተሐውዛ፡ ዕፍረተ መርዓዊ ሥርግው ዘይዛዋዕ በጠረጴዛ፡ ወለተ ጎሊናየ ለከ እንተ አቅረብኩ በጋዛ፡ ምልኣ ለቤተ ነፍስየ ሱርያል ወሬዛ፡ እምአእናፈከ ዘየወጽእ መዐዛ፡፡

፱. ሰላም ለከናፍሪከ እለ ይመስላ ፍጹመ፡ ዘጎብረ ነበልባል ጽጌ ወብቁጸ ፍሕመ፡ እምዮም ሱርያል በከመ ልብየ ዓለመ፡ ኪያከ በታዕካ ሰማይ ረሰይኩ ቃውመ፡ ወበዲበ ምድር አበ ወእመ፡፡

፲. ሰላም ለአፉከ ዘአልቦ ወድኦ፡ ስብሐተ አምላክ ዘልፈ ዘይነብብ በኢያጽርኦ፡ እሰእለከ ሱርያል በግናይ ወአስተብቍዖ፡ ማሕሌተ ገብርከ እመ ሠመርከ እግዚኦ፡ ለቃለ አፉየ ቃልከ ያርትዖ፡፡

፲፩. ሰላም ለአስናኒከ ዘኢይትከሠታ ጊዜ ዛውእ፡ ወኢይፀርሳ በበሊዐ ቆዕ፡ መልአከ ፍሥሓ ወተድላ ሱርያል ራትዕ፡ ኪያከ ዋሕደ እምነ ፀዓድው ስብዕ፡ ጎበ ወልደ ላሜክ ብዙዕ ለአከ እግዚእ፡፡

የማሕሌትህ ስም የዲዳውን አፍ ፈታ፡ መናገር የተሳነውን አንደበትም አናገረ፡፡

7. ለአእዛኒከ፡- ከፈጣሪ አንደበት የወጣውን የሚያስፈራ ነገር ዘወትር ለሚሰሙ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ ለላሜክ ልጅ ምሥጢርን የአስረዳኸው ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከወገኔ የተለየሁ እንደሆነ እኔ የታወቅህ አንተን ተወዳጀሁ፡፡

8. አስተዐ ማሕሌት አቁርብ፡- እንደ ብርና ወርቅ ገንዘብ የከንፈሬን ፍሬ የማሕሌት ግብርን ለፊትህ እኔ በትጋት አቀርባለሁ፤ የሰማይ አደራሽ ሽመላ ሊቅ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከባሕር አሸዋ ላይ የቆመ መብረቅ በተወረወረ የቅናት ፍላጻው እንዳይነድፈኝ ጠብቀኝ፡፡

9. ለአእናፈከ፡- በጠረጴዛ የሚጫዎት የተሸለመ ሙሽራ ሽቶን ፈጽመው ለሚያሸቱ አፍንጫዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ ለአንተ በጋዛ የአቀረብሁትን የጎሊናየን ሴት ልጅ ጎልማሳው ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የነፍሴን ቤት ከከንፈሮችህ ከሚወጣው መዐዛ ምላት፡፡

10. ለከናፍሪከ፡- የነበልባል ጎብር አበባና የተጫረ ፍሕምን ፈጽመው ለሚመስሉ ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከዛሬ ጀምሮ ልቤ እንዳስተማረኝ በሰማይ አዳራሽ አንተን ጠበቃ አደረግሁ፡ በምድር ላይም አባትና እናት አደረግሁህ፡፡

11. ለአፉከ፡- መጨረስ በሌለበት የአምላክን ምስጋና ባለማስታጎል ለሚናገረው አፍህ ሰላምታ ይገባል፤ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! በመገዛትና በመማለድ እልምንሃለሁ፡ አቤቱ የባሪያህን ማሕሌት ከወደድህ የአፌን ቃል ቃልህ ያቅናው፡፡

12. ለአስናኒከ፡- በጨዋታ ጊዜ ለማይታዩ እና ጮርቃ በመብላት ለአልተዳደፉ ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል፤ የተድላ እና የደስታ ቀናተኛው መልአክ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከሰባቱ ነጫጭ አንዱን አንተን ጌታ ወደ ከበረ የላሜክ ልጅ ላክ፡፡

፲፫. ሰላም ለልሳንከ ዘይኤምር ጸታ ሥላሴ፤ ምስለ ካልአኒከ ኀይላት ሶበ ትነቁ ቅዳሴ፤ ጸደፈ መብረቅ ሱርያል እንተ ዘኮንከ ለባሴ፤ በአእጋረ ልብ ዘአልቦ ሕንካሴ፤ አብሐኒ እኪድ አንበሳ ወከይሴ።

፲፬. ሰላም ለቃልከ ከመ ቃለ ማይ ብዙኅ፤ ውስተ እዝነ ኖኅ ዘደምፀ ቅድመ ይዝንም አይኅ፤ እምነ ሊቃናት አሐዱ ሱርያል ፍሡሕ፤ ሶበ ጸዋዕኩከ አስተርእየኒ ከመ ዐርክ ርኅሩኅ፤ በመዓልት ወሌሊት በሥርክ ወበነግህ።

፲፭. ሰላም ለእስትንፋስከ ማእከለ አእናፍ ወአፍ፤ ዘታንሶሱ ዘልፈ እንበለ ዓሪፍ፤ ሱርያል መልአክ ሠረፄ አእላፍ፤ ዕቀበኒ ኢያሕምመኒ አርዌ ተመንግኖ ጽሩፍ፤ ዘአዕይንቲሁ መጥባሕት ወበሊሕ ሰይፍ።

፲፮. ለጕርዔከ ለብርሃነ ስብሐት ምሥራቁ፤ ወለወርቀ ማሕሌት ነፍቁ፤ ለወይነ ጥበብ ሱርያል ማኅየቡ ወዝቁ፤ ማሕሌተ መዝሙር ሶበ ወጠንከ ትሰንቁ፤ ከመ አርጋኖን ጕርዔከ ይነቁ።

፲፯. ሰላም ለክሣድከ ዘኢገዝፈ በትዕቢት፤ ወዘኢተመክሐ ዓዲ በሠርጐ ትርሢት፤ ሱርያል ሥሉጥ በዲበ ኀይላት፤ ንትካየድ በመሐላ ፍቅር እንተ ትጸንእ እሞት፤ አንተ እሳት ወአነ መሬት።

፲፰. ሰላም ለመታክፍቲከ እለ እምኔሆን ሠረፃ፤ መልዕልተ ሉሳሌ አክናፍ ዘያሠርራከ ከመ አኅፃ፤ ሱርያል ዘትቀውም በአርያመ ስብሐት ሕንጻ፤ ማሕሌተ ከናፍርየ ሶበ አኅዛ ያድምጻ፤ ልሳንየ ኮነ ዘይዘብጥ ድኅንጻ።

13. ለልሳንከ፡- ከባልንጀሮችህ ኀይላት ጋር ምስጋናን በምታመሰግን ጊዜ የሥላሴን አካል ለሚያመለክት አንደበትህ ሰላምታ ይገባል፤ የመብረቅ ግምጃን ለባሽ የሆንህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ማንከስ በሌለባቸው የልብ እግሮች አንበሳንና እባብን እረግጥ ዘንድ አሰናብተኝ።

14. ለቃልከ፡- የጥፋት ውኃ ከመዝነቡ በፊት እንደ ብዙ ውኃ ድምፅ በኖኅ ጆሮ ውስጥ ለተሰማው ቃልህ ሰላምታ ይገባል፤ ከሊቃናት አንዱ ደስተኛው ቅዱስ ሱርያል ሆይ! በጠራሁህ ጊዜ እንደ ቸር ወዳጅ በመዓልትና በሌሊት፣ በሠርክና በነግህ ተገለጥልኝ።

15. ለእስትንፋስከ፡- በአፍንጫዎችና በአፍ መካከል ለአለው እስትንፋስህ ሰላምታ ይገባል፤ ዘወትር ያለ ዕረፍት የምትመላለስ የአእላፍ አለቃ መልአኩ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ዐይኖቹ ቢላዋ እና የተሳለ ሰይፍ የሆነ ተሳዳቢው የመተነኳኰል እባብ እንዳያሳምመኝ ጠብቀኝ።

16. ለጕርዔከ፡- የምስጋና ብርሃን ምሥራቅ የማሕሌት ወርቅ ታቦት ለሆነው ጕሮሮህ ሰላምታ ይገባል፤ ለጥበብ ወይን መቅጃው እና እንስራው የሆንህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የምስጋናን ማሕሌት ትመታ ዘንድ በጀመርህ ጊዜ ጕሮሮህ እንደበገና እንደ መሰንቆ ይጮሃል።

17. ለክሣድከ፡- ለትዕቢት ለአልደነደነ እና ዳግመኛም ክብርን በመሸለም ለአልተመካ አንገትህ ሰላምታ ይገባል፤ በኀይላት ላይ የሠለጠንህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! አንተ እሳት እኔ መሬት ሆነን ከሞት በጸናች በፍቅር መሐላ ቃል እንጋባ።

18. ለመታክፍቲከ፡- እንደ ጦር (ፍላጻ) በከፍታ ላይ የሚያበሩህ ክንፎች ከእነርሱ ለበቀለባቸው ትከሻዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ በምስጋና አርያም ሕንፃ ላይ የምትቆም ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከንፈሮቼ ማሕሌትን የአሰሙ ዘንድ በጀመሩ ጊዜ እንደበቴ የበገና መምቻ ሆነ።

፲፱. ሰላም ለእከናፈከ በመልዕልተ መትከፍት እለ ሠረፁ፣ ግቡራት እማንቱ ለመብረቀ ስብሐት እምቀለምጸጽ፣ ሱርያል ረዳኢ ለመልእከ ሰላም ቢጽ፣ ተመሊያሙ ፍርሃተ ለፈድኤትከ እምድምፁ፣ እምቅድመ ገጽየ መናፍስት ይንፍጹ።

19. ለእከናፈከ፡- በትከሻ ላይ ለበቀሉ ክንፎችህ ሰላምታ ይገባል፣ እነዚህም ከምስጋና መብረቅ ብልጭልጭታ የተሠሩ ናቸው፣ የሰላም መልአክ ባልንጀራው ተራዳኢ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከረድኤትህ ድምፅ የተነሣ ፍርሃትን ተመልተው ከፊቴ መናፍስት ይሸሸ።

፳. ሰላም ለዘባንከ ዘይትሞጣሕ መብረቀ፣ በነፋስ ቆራር እንተ ተዐስቀ፣ ሱርያል ዘኮንከ ለርእሰ መዋዕል ልጹቀ፣ ፈጽም ዘኀሊናየ መፍቅደ ወጻሕቀ፣ ጻድቅ መልአክ ዘታፈቅር ጽድቀ።

20. ለዘባንከ፡- በቀዝቃዛ ነፋስ እንደ ወርቅ የተጐነበ መብረቅን ለለበሰ ጀርባህ ሰላምታ ይገባል፤ የርእሰ መዋዕል አንድነቱ የሆንህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! እውነትን የምትወድ እውነተኛው መልአክ ሆይ! የኅሊናዬን ፍላጎት እና ትጋት ፈጽምልኝ።

፳፩. ሰላም ለእንግድዓከ ዘከብዶ ልቡና፤ ሱርያል ርኅሩኅ መልአክ ፍሥሓ ወዳኅና፤ ዘአለበሙኮ ለሄኖክ ዘነገረ ምሥጢር ዜና፤ ህበኒ ኑኃ መዋዕል ወዓዲ ጥዒና፤ ዝንቱ ውእቱ ዘልብየ መና።

21. ለእንግድዓከ፡- ሸክሙ ልቡና ለሆነ ደረትህ ሰላምታ ይገባል፤ የደስታና የድኅነት መልአክ ርኅሩኁ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ለሄኖክ የምሥጢርን ዜና የአስረዳኸው ረጅም ዘመንና ጤና ስጠኝ፤ የልቤ መና ይህ ነውና።

፳፪. ሰላም ለሕፅንከ መዋዕያነ ተወካፌ፤ ወራትዓነ ሐቃፌ፤ ካልዐ ኪሩብ መልአክ ወዘውገ ሱራፌ፤ አርዑተ ፍቅርከ በክሣድየ ትፌ፤ ዲበ አእላፍ ሱርያል ጸሐፌ።

22. ለሕፅንከ፡- አሸናፊዎችን ለሚቀበል ቅኖችን ለሚያቅፍ ጭንህ ሰላምታ ይገባል፤ በአእላፍ ላይ የምትቈጠር የመልአኩ ኪሩብ ኹለተኛው እና የሱራፌ ወገን ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የፍቅርህን ቀንበር በአንገቴ ላይ ጥመድ።

፳፫. ሰላም ለአእዳዊከ ወለእራኃቲከ ዓዲ፤ እለ ተፈጥራ እምነፋስ ወእምነ መብረቅ ነዳዲ፤ ገባሬ ሥምረቱ ሱርያል ለበግዐ ምሥጢር እብኖዲ፤ አድኅነኒ እምረዋዲ ወእምነ ብአሲ ከሐዲ፤ ረድኤተ ዚአከ ዲቤየ አገንዲ።

23. ለአእዳዊከ፡- ከነፋስና ከሚነድ መብረቅ ለተፈጠሩ እጆችህ እና ዳግመኛም ለመሐል እጆችህ ሰላምታ ይገባል፤ የምሥጢር በግ የዕብኖዲ ፈቃድ ፈጻሚ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከከባቢና ከቀማኛ ሰው አድነኝ፤ የአንተን ረድኤትም በእኔ ላይ አኑር።

፳፬. ሰላም እብል ዚአከ መዛርዐ፤ እምነ ቀስተ ብርት ግዱድ እለ ይጸንዓ፤ ርኅሩኃ ልብ ሱርያል ዘኢተአምር ቀጥዐ፤ በለኒ እመ ረከብከኒ እንዘ እቀውም በአፍኣ፤ መካነ ፍሥሓ ወተድላ ፍቁርየ ነዐ።

24. ዘዚአከ መዛርዐ፡- ከተደገነ ከብረት ቀስት ይልቅ የሚበረቱ መዳፎችህን ሰላም እላለሁ፣ ቍጣን የማታውቅ ልበ ርኅሩኁ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! በውጪ ቁሜ ከአገኘኸኝ ‹ወዳጄ ወደ ደስታና ተድላ ቦታ ና› በለኝ።

፳፭. ሰላም እብል ለኵርናዕከ ዘእድ፤ ከመ ኵርናዐ አንበሳ ምርዱድ፤ ሱርያል ዋሕድ እም ሰብዓቱ ነገድ፤ ምጥቀኒ እምቀላየ ወይሌ ዘመዋግዲሁ ክቡድ፤ እግዚእየ ፡ኄር ለገብርከ አብድ።

፳፮. ሰላም ለእመትከ ከመ ዐቅመ ሕለት ከዊኖ፤ ለመቅደሰ ሰማይ ዘይሜጥኖ፤ ሱርያል ፍንው ለረድኤት ወለአድኅኖ፤ ለውኂጦትየ ከይሲ ሶበ ለውለወ ልሳኖ፤ ሰይፈ እዴከ ይምትሮ ወይቀጥቅጥ ቀርኖ።

፳፯. ሰላም ለእራኅከ ዘይትሜጠ ጸሎቶሙ፤ ለየዋሃነ ነፍስ ኵሎሙ፤ ሱርያል ፍንው ፡ነበ ወልደ ላሜሕ ቀዲሙ፤ ከመ ይኩነኒ ግርማ ለድማኅየ በፍጽሙ፤ ለእራኃ እዴከ ዘልፈ ይሠየም ማኅተሙ።

፳፰. ሰላም ለአጻብዒከ ጽሉአ ዘኢገሠሣ፤ ኢይርሳሓ ጥቀ ወከመ ኢይርኰሳ፤ በሐብለ ፍቅርከ እብል ዘተሠገርኩ እንስሳ፤ ምእመነ ነፍስየ ሱርያል ሐዊሳ፤ እንተ ኢተጽሕፈ ላዕሌከ አበሳ።

፳፱. ሰላም ለአጽፋረ እዴከ እለ ኀቡራት በሥን፤ ወግብረቶን ብዑድ እምእሳተ ሕይወት ርሱን፤ በምሥዋዐ አብ ቀዋሚ ሱርያል ካህን፤ ለለ ጸዋእኩ ነዐ በውስተ ኵሉ መካን፤ ፡ነበ ዘከርኩ ስመከ ኢይቅረብ ሰይጣን።

፴. ሰላም ለገበዋቲከ እለ ይትዐፀፉ ነበልባለ፤ ከመ ፀምር ወዓጌ እንተ ኢኮነ ፍቱለ፤ ሱርያል ርኅሩኅ እንተ ኢተአምር በቀለ፤ ጸግወኒ ለነባሪ ሰላመ ወሣህለ፤ ወእመ አኮ መዐድመ ቃለ።

25. ለኵርናዕከ፡- እንደ አንበሳ ክርን ለጠነከረው ለእጅህ ክርን ሰላም እላለሁ፣ ከሰባቱ ነገድ አንዱ የሆንህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ቸሩ ጌታዬ ሰነፉ ባሪያህን ሞገዱ ከከበደ የልቅሶ ቀላይ ነጥቀህ አውጣኝ።

26. ለእመትከ፡- እንደ ዘንግ ልክ ሆኖ የሰማይን መቅደስ ለሚለካው ክንድህ ሰላምታ ይገባል፤ ለመራዳትና ለማዳን የምትላክ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! እባብ እኔን ለመዋጥ ምላሱን በአውለበለበ ጊዜ የእጅህ ሰይፍ ይቁረጠው፣ ቀንዱንም ይቀጥቅጠው።

27. ለእራኅከ፡- የኹሉንም የነፍስ የዋሃን ጸሎታቸውን ለሚቀበል መሐል እጅህ ሰላምታ ይገባል፤ ቀድሞ ወደላሜሕ ልጅ የተላክህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ግርማ ይሆነኝ ዘንድ የመሐል እጅህ አሻራው (ማኅተሙ) በመሐል ራሴ ላይ ዘወትር ይቀመጥ።

28. ለአጻብዒከ፡- እንዳይገሰቁሉ እና እንዳይረክሱ የተጠሉ ነገሮችን ለአልዳሰሱ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ በፍቅርህ ገመድ የተያዝሁ እንስሳ እኔ በአንተ ላይ በደል የአልተጻፈ የነፍሴ መታመኛ ቅዱስ ሱርያል ፍቅር ነው እላለሁ።

29. ለአጽፋረ እዴከ፡- በውበት ለተባበሩ ተፈጥሮአቸው ከጋለ ከሕይወት እሳት ለተለዩ ለእጅህ ጣቶች ሰላምታ ይገባል፤ በአብ መሠዊያ ላይ የቆምህ ካህን ቅዱስ ሱርያል ሆይ! በኹሉ ቦታ ስጠራህ ፈጥነህ ና፣ ስምህን በጠራሁበትም ሰይጣን አይቅረብ።

30. ለገበዋቲከ፡- እንደ ግምጃና ጥጥ የአልተፈተለ ነበልባል ለሚታጠቁ ጦኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ በቀልን የማታውቅ ርኅሩኅ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ለደጅ ጠኚህ ለእኔ ሰላምንና ይቅርታን ስጠኝ፤ ያም ባይሆን የሚወደድ ቃልን ስጠኝ።

፴፩. ሰላም ለከርሥከ በወርቀ ይዋሂ ልቡጥ፣ ሥርናየ ርኅራኄ ወግህል ውስቴቱ ስጢጥ፣ በዲበ አእላፍ ጎይላት ሱርያል ሥሉጥ፣ አድኅንኒ እምነ አርዌ ዘይመውእ በሐይጥ፣ እስመ ኢይጠብብ አነ እምጻድቅ ሎጥ።

31. ለከርሥከ፡- የርኅራኄ እና የይቅርታ ስንዴ በውስጡ ለተጨመረ በደግነት ወርቅ ለተለበጠ ሆድህ ሰላምታ ይገባል፣ በአእላፍ ጎይላት ላይ የሠለጠንህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! እኔ ከሎጥ ይልቅ ብልሃተኛ አልሆንምና በሽንገላ ከሚያሸንፍ አውሬ አድነኝ።

፴፪. ሰላም ለልብከ መካነ እለምሮ ወጥበብ፣ ወዘርኅራኄ መዝገብ፣ ሱርያል መልአክ ብእሴ ነደ እሳት ልሁብ፣ ኪያከ ለናገዞ ምድር ዘፈነወ አብ፣ በዕለተ ተአስረ መስሐቲ ኮከብ።

32. ለልብከ፡- የዕውቀትና የጥበብ ቦታ እና የርኅራኄ ሳጥን ለሆነው ልብህ ሰላምታ ይገባል፤ የወዛ የነደ እሳት ሰው መልአኩ ቅዱስ ሱርያል አሳቹ ኮከብ በታሰረ ቀን ምድርን ለማረጋጋት አብ የላከህ አንተ ነህ።

፴፫. ሰላም ለጎሊናከ ዘያስተጋብእ አእምሮ፤ ለጥበብ ጎራት ውስተ ዐጸዳ ወፌሮ፤ ገጻተ ሥላሴ ሱርያል ዘትኤምኅ ጊዜ ዘምሮ፤ ማሕሌተ ስምከ እመ አፍቀርኩ አፍቅሮ፤ ባርክ አሥምሮ ወአብዝኅ ማእረሮ።

33. ለጎሊናከ፡- በተመረጠች ጥበብ ቦታ ውስጥ ተሰማርቶ ዕውቀትን ለሚሰብሰብ ጎሊናህ ሰላምታ ይገባል፤ በምስጋና ጊዜ የሥላሴን አካል እጅ የምትነሣ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የስምህን ማሕሌት መውደድን ከወደድሁ ዘንድ መወደዱን ባርክ፣ አዝመራውንም አብዛ።

፴፬. ሰላም ለንዋየ ውስጥከ ዘግብረቶን ምሥጢር፤ ወሥነ ኅበሪሆን ሥዉር፤ ሰባኬ ዳኅና ሱርያል ቅድመ ድምሳሴሃ ለምድር፤ እመ ተንሥአ ላዕሌየ ጎይለ ጸላዒ ወፀር፤ ከመ ጢሰ እቶን ይዝርዎ ሐፅከ ዘንጥር።

34. ለንዋየ ውስጥከ፡- ተፈጥሮአቸው ምሥጢር የኅብራቸው ውበት ድብቅ ለሆኑ ለውስጥ አካሎችህ ሰላምታ ይገባል፤ ከምድር ጥፋት በፊት የድኅነት ሰባኪ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የጠላቶች ጎይል በላየ ላይ ከተነሣ የብልጭታ ጦርህ እንደ ምድጃ ጢስ ይበትነው።

፴፭. ሰላም ለኅንብርትከ ዘቦቱ መካነ፤ ምስለ ከርሥ ሐቋ ኅበ ተወሰነ፤ ሱርያል ወሬዛ ዘረሰይኩከ ምእመነ፤ ናቅም ባሕቲትነ አንተ ወአነ፤ ከመ እንተ ሞት ጽኑዐ ኪዳነ።

35. ለኅንብርትከ፡- ከሆድ ጋር ወገብ በተወሰነበት ቦታ ለአለው እምብርትህ ሰላምታ ይገባል፤ መታመኛ የአደርግሁህ ኅልማሳ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! እንደ ሞት የጸና ቃል ኪዳንን አንተና እኔ ብቻችንን እናጽና።

፴፮. ሰላም ለሐቋከ ዘወርቀ አፈዝ ቅናቱ፤ ወጽንዐ ጎይልከ ዓዲ ዘጎዱር ውስቴቱ፤ ሱርያል አንተ አሐዱ እምነ ፀዓድው ሰብዓቱ፤ እመ ፈጸምከ ዓሕቅየ ዘጎሊናየ ይፈቱ፤ ከመ ፍቁርከ አነ አእምር በዝንቱ።

36. ለሐቋከ፡- ትጥቁ የአፈዝ ወርቅ ለሆነለት እና ዳግመኛም የጎይልህ ብርታት በውስጡ ለአደረበት ወገብህ ሰላምታ ይገባል፤ ከሰባቱ ነጫጮች አንዱ አንተ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ጎሊናዬ የሚወደውን ፍላጎቴን ከፈጸምህልኝ እኔ ወዳጅህ እንደሆንሁ በዚህ ዐውቃለሁ።

፴፯. ሰላም ለአቍያጺከ እለ ተሣረራ ወተነድቃ፤ ምስለ ሐቋ ወአብራክ እንዘ

37. ለአቍያጺከ፡- ከወገብና ከጕልበቶች ጋር አንድ ሆነው ለተሠሩና ለተመሠረቱ ጭኖችህ ሰላምታ ይገባል፣ የሰማይ አደራሽ ሽመላ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከሚተነኳኰል

ይትላጸቃ፤ ለታዕካ ሰማይ ሱርያል ማዕንቃ፤ ከመ ትባልሐኒ አበ ትምይንት ቤቃ፤ ታስተብቍዓከ ነፍስየ ጽሒቃ፡፡

ቁ፰. ሰላም ለአብራኪከ በታዕካ ሰማይ እለ ይሰግዳ፤ ጊዜ ታቀርብ ለአምላክ መዝሙረ ስብሐት ወጋዳ፤ ከመ አስሐትያ ሱርያል ዘአርኢየከ ጸዐዳ፤ ፈጽም እግዚእየ ለኅሊናየ መፍቅዳ፤ ወለጸሎትየ ታጸንሕሕ ሰዳ፡፡

ቁ፱. ሰላም ለአእጋሪከ በገጸ ፀባዖት እለ ይቀውማ፤ ጊዜ ትነቁ ማሕሌተ ሐዋዝ ዜማ፤ ሱርያል ክሉል በዕበየ ሞገስ ወግማ፤ ባልሐኒ ለለ ጽባሑ እምእደ መኰንን መስቴማ፤ ለነፍሰ ዚኣየ ዘይጸልእ ሰላማ፡፡

፵. ሰላም ለሰኳንዊከ በዐጸደ አምላክ እለ ያነሰሐልላ፤ እንዘ ይትከዋዋ ውስተ ርኅበ ዓለም ኵላ፤ ሱርያል ርኅሩኅ መልአከ ፍሥሓ ወተድላ፤ በውስተ ርእስከ ዘሀሎ ቀጸላ፤ እምስነ ኦርያሬስ ይበርቅ ወይልሒ እምእብላ፡፡

፵፩. ሰላም ለመከየድከ ዘኢይደክማ እምቀዊም፤ ጊዜ ትነቁ ዝማሬ በዐጸደ አምላክ ግሩም፤ በዲበ አእላፍ ኀይላት ሱርያል ስዩም፤ በእንቲኣከ እግዚኦ ይዳደቀኒ እምዮም፤ መፍቀሪተ ነጽሕ ሰላም ወእኅታ ጾም፡፡

፵፪. ሰላም ሰላም ለአጻብዒከ ዘአእጋር፤ ዘፍቅደ ጾታሆን ዐሥር፤ እምነ ነፋስ ወንጥር ሱርያል ግቡር፤ ዕቀበኒ ኢይምሥጠኒ በኵሉ አሚር፤ ከመ እንተ ነምር ዘኮነ ነገር፡፡

፵፫. ሰላም ለአጽፋረ እግርከ ግቡራት እምዋዕይ፤ ሱርያል መልአክ ግሩመ ራዕይ፤ አመ ተደምሰሰ ኵሉ ዘታሕተ ሰማይ፤

ታድናት ዘንድ ነፍሴ አባቴ ሆይ! እያለች ተግታ ትማልድሃለች፡፡

38. ለአብራኪከ፡- የምስጋና መዝሙር እጅ መንሻን ለአምላክ በምታቀርብ ጊዜ በሰማይ አዳራሽ ለሚሰግዱ ጕልበቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ አርአያህ እንደ ውርጭ ነጭ የሆነ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! አቤቱ የኅሊናዬን ፈቃድ ፈጽምልኝ፤ ታሻትታት ዘንድ ጸሎቴንም ውሰዳት፡፡

39. ለአእጋሪከ፡- የሚያምር ዜማ ማሕሌትን በምታሰማ ጊዜ በፈጣሪ ፊት ለሚቆሙ እግሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ በመወደድና በመፈራት ከፍታ የተጋረድህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የነፍሴን ሰላሟን ከሚጠላ ከገዥ ሰይጣን እጅ በየጊዜው ጠብቀኝ፡፡

40. ለሰኳንዋክ፡- ለመላዋ የዓለም ስፋት ውስጥ እየፈጠኑ በአምላክ ቦታ አለል ዘለል ለሚሉ ተረከዞችህ ሰላምታ ይገባል፤ የደስታና የተድላ መልአክ ርኅሩኅ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! በራስህ ላይ ያለው ሻሽ ከፀሐይ ውበት ይልቅ ያበራል፣ ከጨረቃም ይልቅ ያምራል፡፡

41. ለመከየድከ፡- በሚያስፈራ በአምላክ ቦታ ምስጋናን በምታሰማ ጊዜ ከመቆም የተነሣ ለማይደክሙ መረገጫዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ በአእላፍ ኀይላት ላይ የተሾምህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! አቤቱ ስለ እንተ ከዛሬ ጀምሮ የንጽሕና ወዳጅ ሰላምና እኅቷ ጾም ያግኙኝ፡፡

42. ለአጻብዒከ፡- የወገኖቻቸው ቍጥር ዐሥር ለሆኑ ለእግሮችህ ጣቶች ሰላምታ ይገባል፤ ከነፋስና ከመብረቅ የተፈጠርህ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! እንደ ነብር ያለ የሆነ ነገር እንዳይነጥቀኝ በኹሉ ጊዜ ጠብቀኝ፡፡

43. ለአጽፋረ እግርከ፡- ተፈጥሮአቸው ከብርሃን ለሆኑ ለእግርህ ጥፍሮች ሰላምታ ይገባል፤ መልኩ የሚያስፈራ መልአኩ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከሰማይ በታች ያለው ኹሉ በተደመሰሰ ጊዜ ጠባቂ የሆንኸው ማዕበል እየሆነ ካለው

ዐቃቤ ዘኮንከ በመስቀረ ዕፁ ዓባይ፤ ለብእሲ ንሁይ እምዘ ያመዓብል ማይ፡፡

ሣ፬. ሰላም ሰላም ለሥነ ቆም እብሎ፣ ዘይበርቅ በአንበልብሎ፣ ሱርያል ፍንው ለድኂን ወለታሣህሎ፣ ለዘይትበኣሰኒ በተኀይሎ፣ ለአርዌ ኀጢአት አቍስሎ፣ እምገጽየ ይንፍጽ ወይርከብ ተኀጕሎ፡፡

ሣ፭. ሰላም እብል ለመልክዕከ መክብቦ፤ መዓንዝረ ለንጻስ ዘይገለብቦ፤ ሱርያል ሳውዕ መሥዋዕተ የብቦ፤ አስተዋርሰኒ በትንባሌከ ለኅቡዓተ ጽድቅ መዝገቦ፤ በኀበ አምላክከሰ ዘይሰዓን አልቦ፡፡

ኦ አምላከ ቅዱስ ሱርያል ዕቀበኒ ወአድኅኒ እስመ አነ ኀጥእ ወአባሲ ጸሐፌ መዝግብ ወልደ ትንሣኤ፤ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቡነ ዘበሰማያት...

✝ ✝ ✝

ውኃ ያረፈን ሰው በታላቂቱ የዕንጨት መርከቡ (ታንኳ) ጠባቂ የሆንኸው አንተ ነህ፡፡

44. ለሥነ ቆምከ፡- በመንቦግቦግ ለሚፈልቀው ለቁመናህ ውበት ሰላምታ ይገባል እላለሁ፣ ለድኅነትና ለይቅርታ የምትላክ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! ከፊቴ ይሸሽ ዘንድ ጥፋትንም ያገኝ ዘንድ በመበረታታት የሚጣላኝን የኀጢአት አውሬ አቍስለው፡፡

45. ለመልክዕከ፡- የወርቅ ግምጃ መዘራዝር የሚጋርደው የመልክህን ክብነት ሰላም እላለሁ፤ የምስጋና መሥዋዕት ቄስ ቅዱስ ሱርያል ሆይ! የጽድቅ ሥውር መዝገብን በምልጃህ አዋርሰኝ፤ በአምላክህ ዘንድ የሚሳን ነገር የለምና፡፡

አቤቱ የቅዱስ ቅዱስ ሱርያል አምላክ ሆይ! እኔን ባሪያህን..... ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድነኝ ጠብቀኝም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

አባታችን ሆይ!...

✝ ✝ ✝